# የማሰር ባህል

መስፍን ወልደ ማርያም

ግንቦት 2000

በጥንቶቹ መሳፍንት ዘመን ለሥራ የአንድ ቡድን መሪ ሆኜ ወደጎሐ ጽዮን ሄጄ ነበረ፣ የማላውቃቸው የወረዳው አስተዳዳሪ የሆኑ አንድ ባላምባራስ መኪና ውስጥ ተቀምጬ ከሰው ጋር ስነጋገር አዩኝና አልወደዱልኝም፣ ‹ማነው ይሄ; ምንድነው የምታነጋግረው;› እያሉ ሰውዬውን ሲቆጡ ከመኪና ወረድሁና ማንነቴን ገለጽሁላቸው፣ ደብዳቤም አሳየሁአቸው። ከምመራው ቡድን ውስጥ አንድ አሜሪካን አይተዋልና መሪው እኔ ነኝ ስላቸው በጣም ተናደዱ ‹ይሄ ደፋር ፈረንጅ እያለ መሪው እኔ ነኝ ይላል;› ብለው ወደፖሊሱ ዞሩና ውሰደው፣ እሰርልኝ!› አሉት። ፖሊሱ ግራ ገባውና ያለደብዳቤ አላስርም አለ፣ ምን ችግር አለ; ወረቀት እንዲመጣላቸው አዘዙና ባቡር መንገድ ላይ ቁጭ ብለው ጻፉለት፣ ፖሊሱ ይዞኝ ሄደ፣ አንድ ቀን አደርሁ። እንግዲህ ይሄ ሕግ ነው; ወይስ ጉልበተኛነት ነው፣ ጉልበት የሆነላቸው ፖሊስ ነው እንጂ እሳቸውማ በጉልበት ለእኔ አይበቁም ነበር። በኢትዮጵያ ሰውን ማሰር እንዲህ ቀላል ነበር፣ አሁንምነው።የጉልበት መግለጫ ከመሆን በቀር ሌላ ዓላማ የለውም። ይህ አጉል የጉልበት መግለጫ አንዱ የባህል መሠረት ሆኖ በጣም ስለተዋኀደን አብሮን የተፈጠረ ይመስላል፣ የሚያስረው መንግሥት ወይም ፍርድ ቤት ብቻ አይደለም፣ ወላጆችም ያስራሉ፣ ጌቶችም ያስራሉ፣ ማንም ሹም ነኝ ባይ ያስራል፣ በደርግ ዘመን ቀበሌው ሁሉ እንደፈለገው ማሰር ስለጀመረ ቀበሌዎች ሰው እንዳያስሩ የሚል ትእዛዝ ተላልፎላቸው ነበር። ማሰር የጥፋት ውጤት ሳይሆን ልዩ ደስታን የሚሰጥ የጉልበት መግለጫ ነው። የጉልበት መግለጫው መሠረቱ ከባድ የሚያቃዠ ፍርሃትና ስጋት ነው። በጥንት ዘመን የሥልጣን ተቀናቃኝ ይሆናሉ ተብለው የሚፈሩት የነገሥታት ልጆች በየተራራው ላይ ወህኒ ቤት ውስጥ ያለምንም ጥፋት ይኖሩ እንደነበሩ እናውቃለን፣ እንዲያውም በዘመናችን የልጅ ኢያሱ ወንዶች ልጆች ሁሉ በሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ በግዞት ሲኖሩ አይተናል። አሳፋሪ የፍርሃት በህል ነው፣ ገና አልለቀቀንም።

በመሠረቱ መታሰር ቅጣት ነው; አንዳንዴ መታገት ይባላል፣ የሚያስረው ወይም የሚያግተው ማን ነው? የሚታሰረው ወይም የሚታገተውስ ማን ነው? ያለምንም ጥርጥር ለማገት ወይም ለማሰር ጉልበት ያስፈልጋል፣ ያለምንም ጥርጥር የሚታሰረው ወይም የሚታገተው ሰው የጉልበተኞቹ ዓይን ያረፈበት መሆን አለበት።

ከሕግ ጋር ምንም ዝምድና የለውምና በማገቱ እንጀምር፣ በአሜሪካና በኢጣልያ ብዙ የወንጀል ድርጅቶች አሉ፣ በጉልበታቸው ከመንግሥት ጋር የሚፎካከሩ ናቸው፣ ያልገበረላቸውን እንካን ማገትና ማሰቃየት እስከመግደልም ይደርሳሉ። በጣም ሀብታሞች ስለሆኑም ፖሊሶችንም ሆነ ዳኞችን በገንዘብ እየገዙ ተግባራቸውን በትክክል እንዳይፈጽሙ ያደርጋሉ። እነዚህ የወንጀል ድርጅቶች ከሕግ ውጭና ከሕግ በላይ ሆነው በራሳቸው ኃይል ለራሳቸው ጥቅም የሚሠሩ ናቸው፣ ስለዚህም የነዚህ የወንጀል ድርጅቶች ተግባር በመሠረቱ ጸረ-ማኅበረሰብና ጸረ-ሕግ መሆኑን እናውቃለንና ሰዎችን በማገታቸው አንደነቅም ይሆናል።

WWW.MESFINWOLDEMARIAM.ORG

ማኅበረሰቡ በተደራጀበትና መንግሥት ባለበት አገርስ ሰዎች የሚታሰሩት እንዴት ነው? አንድ ሰው ወንጀል ሲፈጽም እጅ-ከፍንጅ ከተያዘ ለጊዜው በመደበኛ ፖሊስ ይያዝና ይታሰራል፤ ሆኖም ከአርባ ስምንት ሰዓታት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ፖሊስ እስረኛውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፤ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ለመወሰን ሁለት ምርጫዎች አሉት፤ አንዱ የታገተውን ሰው በዋስ መልቀቅ፡ ሁለተኛው ደግሞ ታስሮ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት።

የሚገቱት ወይም የሚታሰሩት ሰዎች ዓይን ያረፈባቸው ሊሆኑ ይችላሉ ብያለሁ፤ እነዚህ ሰዎች ከጥፋት የሚቆጠርባቸው (ወንጀላቸው አልልም) የሌላውን ሰው ቀልብ መሳባቸው ብቻ ሊሆን ይችላል፤ ‹‹ጅብ የሚጠራባቸው›› ሀብታቸው ሊሆን ይችላል፤ ዝናቸውም ሊሆን ይችላል። ዘፋኝ በዘፈኑ ሲታሰር አይተናል። ሠልጥነናል ስንል በዚህ ረገድ የአፄ ቴዎድሮስን ያህል የመቻል ብቃት አናሳይም፤ በየሄዱበት እየተከተለች ከነዘርዘራቸው በግጥም ስትሰድባቸው የነበረችውን አዝማሪ አልነኩዋትም። በዘመናችን ዘፋኝ ብቻ ሳይሆን ዘፈንም ሲታሰር አይተናል። በባህላችን ሀሳባቸውን የመግለጽ ነጻነት የተፈቀደላቸው አዝማሪዎች፡ አልቃሾችና እረኞች ነበሩ ሲባል ሰምቻለሁ። መንገዳችን ወደኋላ ሆነና ፈረንጆች ቀደሙን።

ለመሆኑ የማያጠራጥር ተጨባጭ ማስረጃ ሳይገኝ ሰውን ማሰር ምን ይባላል; ሰዎችን አስሩ በኋላ ምርመራ ምን ማለት ነው; አሥር ዓመትና ከዚያም በላይ ከታሰሩ በኋላ ፍርድ ቤት ወይ በነጻ የሚያሰናብታቸው ወይም ደግሞ ያንኑ በእስር ላይ የቆዩበትን ያህል ጊዜ እስራት ሲፈርድባቸው ምን ይባላል;

በጣም የሚደንቀው ነገር ደግሞ እስር ቤቶች በውጭ እርዳታ የሚደጎሙ መሆናቸው ነው፤ አለዚያማ እስረኛው በችጋርና በበሽታ ያልቅ ነበር። ሆኖም ትንሽም ቢሆን ለእስር ቤቶች የሚወጣው የሕዝብ ገንዘብ ለዚች ለደሀ አገር ጉዳትን የሚያስከትል ነውና የዋስትና መብት የሚጠበቅ ቢሆን ከብዙ ወጪ እንድናለን። እስር ቤቱን ለማሙዋሙዋቅ ተዘጋጅተው ክረምቱን በዚያ ለማሳለፍ የሚገቡት ‹‹ደንበኞች›› የሚባሉት ይበቃሉ። የሁለት ሺህ ዓመታት በዓል ጊዜ ሳያልፍ የማሰርን በህል ከላያችን እናራግፈው፤ ከሱም ጋር ፍርሃታችንንና ስጋታችንን ለመጋፈጥ መንፈሳዊ ወኔ እናዳብራለን።